ባሕረ ሐሳብ

ዘዘመነ ሉቃስ ፳፻፲፱ ከነታሪኩ



አዘጋጅ፡- መምህር ቡሩክ ወርቅነህ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር
መጽሐፈ ባሕረ ሐሳብ ዘተናገሮ ቅዱስ ድሜጥሮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘለእስክንድርያ።

በአብ ስም አምነን አብን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን ሠራዒ ብለን ምንም ለአጠይቆተ አካላት ሠለስቱ አካላት በስም በግብር በአካል ሦስት ብንል በባሕርይ በህልውና በፈቃድ አንድ አምላክ ብለን አንድም አብ ልብ ወልድን ቃል መንፈስ ቅዱስን እስትንፋስ ብለን ምንም ለአጠይቆተ አካላት በስም በአካል በግብር ሦስት ብንል በመለኮት በሥልጣን በአገዛዝ አንድ ብለን ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ባሕረ ሐሳብን እንጀምራለን። ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ እንጀምራለን አለ ስንኳን መንፈሳዊ ሥራ ሥጋዊ ሥራ ቅሉ አርስ እቆፍር፣ እጽፍ እደጉስ፣ ቢሉ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይፈጸምምና ኩላኬ ፍድፋዴ እንተ ይገብራ ብእሲ ኢትትፈጸም ዘእንበለ በረድኤተ እግዚአብሔር በከመ ቃሉ ለእግዚእነ እስመ ዘእንበሌየሰ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ ወኢምንትኒ እንዲል ወኢምንተኒም ይላል ዮሐ. ፲፭፣፭። ባሕረ ሐሳብ አለ ሐሳበ ባሕር ሲል ነው የተዘዋወረ ቀለም ነው ባሕር ያለው ዘመን ነው እስመ በመዳልው ደለወ ዓለመ ወበመስፈርት ሰፈራ ለባሕር ለባሕርከኒ አልቦቱ መጠን (ሐሳብ) እንዲል። ሐሳብ ያለው ቁጥር ነው ኢትትሐሰብዎሙ ወርቆሙ ወብሩሮሙ፣ ወእለ ኢሐሰበ ሎሙ ኵሎ ጌጋዮሙ እንዲል መዝ. ፴፩፣፩።

ቦ እንዳለው ይሆናል ባሕረ ሐሳብ ማለት ቁጥር ያለው ዘመን ማለት ነው። ይህስ እንደምነው ቢሉ ዘልማዱ ጎሩት የተባለ ጌታ እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም እንዲህ እንደዛሬው ሁሉ በአንድነት በሥስትነት ሲሠለስ ሲቀደስ ይኖር ነበር ቅድመ ዓለም ፍጥረት ሳይኖር ማን ያመሰግነው ነበር ቢሉ ምሥጋና የባሕርዩ ስለሆነ አንድም ዛሬ የሚመሰገነው አካሉ ቅድመ ዓለም የነበረ ስለሆነ እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ስብሐቲሁ ዘተጸርዐ አላ ምሉዕ ውእቱ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዲል ቅዳሴ ሠለስቱ ምእት።

ከዚህ በኋላ ክብሩ በባሕርዩ እንደቀረ አውቆ ዓለምን ልፍጠር ብሎ አሰበ አስቦም አልቀረ ፈጠረ ሰውንና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ፈጠረ የቀረውን ፍጥረት ግን ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ሊሆን ፈጠረ ወኵሉ ዘተፈጥረ ለመፍቅደ ነባብያን ቦ እምኔሆሙ ለምህሮ ወቦ እምኔሆሙ ለተዘክሮ እንዲል አረጋዊ መንፈሳዊ። እግዘአብሔር የፈጠረው ፍጥረት እያንዳንዱ ቢቆጠር ፍጡር ተናግሮ ባልፈጸመውም ነበር ነገር ግን ሁሉን እየወገኑ ብዙውን አንድ ብዙውን አንድ እያሉ ቢቆጥሩ ከእሑድ እስከ ዐርብ የፈጠረው ፍጥረት ፳፪(22) ነው።

፳፪(22)ኛውም አዳም ነው ጌታ አዳምን በነፍስ በሥጋ ሕያው አድርጎ ፈጥሮ በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ ከአንዲት ዕፀ በለስ በቀር ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን ሁሉ ብላ ጠጣ ግዛ ንዳ ብሎ በገነት አኖረው እርሱም ፯(7) ዓመት ከሁለት ወር ከአስራ ሰባት ቀን በሕጉ ጸንቶ ኖረ ኩፋ፬፣፲፯። ከዚህ በኋላ ግን ምክረ ከይሲን ሰምቶ አምላክነትን ሽቶ ዕፀ በለስን በልቶ ከፈጣሪ ተጣልቶ ከገነት ወጣ ጌታም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ገሀነምን ፈረደበት።

አዳምም በፈታሒነቱ አንጻር መሐሪነቱ እንዳለ አውቆ ንሥሐ ገባ ንሥሐ ቢገባ በኃጢአ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድህክ ውስተ መርጎብከ ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበሞትየ ብሎ ተስፋውን ነገረው (ቀሌምንጦስ)። አዳምም ይህን ተስፋ ሰምቶ ለልጆቹ ነገራቸው ልጆቹም ይህን ተስፋ ይዘው እኩሉ በፀሐይ እኩሉ በጨረቃ እኩሎቹም በከዋክብት ሲቆጥሩ ኖሩ ነቢያትም ከዚህ አያይዘው ትንቢት ሲናገሩ ሱባዔ ሲቆጥሩ እስከ ዘመነ ሥጋዌ ደረሱ ቁጥር የተጀመረበት ምክንያቱ ይህ ነው።

ከዚህ በኋላ የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሣ አምላክ ቅድመ ዓለም በልቡና ያሰበውን ድኅረ ዓለም በነቢያት ያናገረውን ይፈጸም ሰው ሆነ ሥጋ ለበሰ ሰው ሆኖም ሕግ ጠባይዓዊን ሕግ መጽሐፋዊን ሲፈጽም አደገ። ሕግ ጠባይዓዊ አበ እመ ማለት፣ ጸጉር ጽሕም ጥፍር ማብቀል፣ ለእናት ለአባት መታዘዝ፣ በየጥቂቱ ማደግ ነው ልህቀ በበሕቅ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ እንተ ይእቲ እሙ እንዲል ወለይእቲ እሙም ይላል። ሕግ መጽሐፋዊ በ፵ ቀን ወደ ግዝረት መግባት፣ በ፵(40) ቀን እጉለ ርግብ ዘውገ ማዕነቅ ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ መግባት፣ በዓመት ፫(3) ጊዜ ለበዓል ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት ነው ለያስተርኢ ተባእተከ ሥልሰ ጊዜያተ ምዕረ በበዓመት ወዘኢዐርገ ለበዓል ርጉም ውእቱ እንድትል ኦሪት። እግዘኣ ለኦሪት ገብረ በውስተ ኦሪት ከመ ይሳየጦሙ ለእለ ውስተ ኦሪት እንዲል። ገላ ፬፣፬: ዘሌ ፲፪።

ጌታ በ፲፪(12) ዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ መውጣቱም ለማስተማር ነው እንጂ ለሌላ አይደለም። በሌሎች ግን ከ፳(20) ዓመት በታች እንዳይወጡ ሥርዓት ተሠርቶባቸዋል እሱ ግን በ፲፪(12) ዓመቱ ወጥቷል እንዲህም አድርጎ ፴(30) ዓመት ሲሞላው በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ አብ በደመና ሆኖ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ብሎ መሰከረለት መንፈስ ቅዱስም በአምሳለ ርግብ ወርዶ ከራሱ ላይ ተቀመጠ ወልድ በክበበ ትስብእት ተገለጠ ሰማይ ተከፈተ ምሥጢር ተገለጠ አንድነት ሦስትነት ታወቀ ማቴ፫ የባሕርይ ልጅነቱን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ካስመሰከረ በኋላ አልዋለም አላደረም ዕለቱን ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ፵(40) መዓልት፣ ፵(40) ሌሊት ጾመ።

መዋዕለ ጾሙን ሲፈጽም ሰይጣን በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ፈተነው። በስስት፣ በትዕቢት፣ በፍቅረ ንዋይ ጌታም በሦስት ወገን ድል ይነሣዋል በስስት የመጣውን በትዕግስት በትዕቢት የመጣውን በትሕትና በአፍቅሮ ንዋይ የመጣውን በጸሊዐ ነዋይ ድል ይነሣዋል ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ የሚሰኙ እኒህ ናቸው። ዛሬም ሰው እነዚህን ድል ከነሣ ሌሎች ኃጣውእ አይቆሙበትም አይቀዋወሙትም። ሰይጣንን ድል ነሥቶ ከዚያ ወጥቶ ምድረ እስራኤል ገብቶ ትምህርት ተአምራት ጀመረ የእጁን ተአምራት አይተው የቃሉን ትምህርት ሰምተው ከአሥር አህጉር ከብዙ መንደር ተወጣጥተው የአምስት ገበያ የሚያህል ሰዎች ተከተሉት ከእነዚያም ፻፳(120) ቤተሰብን ይመርጣል መጀመሪያ ፲፪ቱን(12) ሐዋርያት መረጠ ወጎረየ እምሰብአ ዚኣሁ ፲ወ፪ተ ሐዋርያተ እንዲል ቀጥሎ ፸፪ቱን(72) አርድእት መረጠ ወረሰየ ካልዓነ ሰብአ እንዲል ፎም ይላል በአጎዙ ቀጥሎም ፴፮ቱ(36) ቅዱሳት አንስትን መረጠ ፻፳(120) የጌታ ቤተሰብ የሚሰኙ እነዚህ ናቸው

እነዚህም ከዋለበት ይውላሉ ካደረበት ያድራሉ ትምህርት ተአምራት አይከፈልባቸውም ሌሎችን ግን ምሽት ይከለክላቸው ነበር።

ከዚህ በኋላ ለ፲፪ቱ(12) ነገደ እስራኤል ወር ወር ዕጻ እየገባ ይሰብክላቸው ነበር ፫(3) ዓመት ከ፫(3) ወር ወንጌልን አስተማረ ትምህርቱ በምር ሲረዳለት ለመድኃኒተ ዓለም በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ተሰቀለ ምነው ሌሎች ብዙ መካናት አልነበሩምን ስለምን በቀራንዮ ተሰቀለ ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ይደርስ ይፈጸም ዘንድ ነው ትንቢት ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር ተብሎ ተነግሯል መዝ ፸፫፣፲፪ እርሱም ባለቤቱ ኢይደልዎ ለነቢይ መዊት በአፍኣ ዘእንበለ በኢየሩሳሌም ብሏል ምሳሌውም አዳምን ያሳተ ርእሰ ከይሲ ከዚያ ወድቆ ነበርና እርሱን ፈጽሞ ድል እንደነሣው ለማጠየቅ ትንቢቱን ባወቀ አናግሮታል ምሳሌውንም እንጂ እርሱ ባወቀ አስመስሎታል። ምሥጢሩ እንደምን ነው ቢሉ አፅመ አዳም ከዚያ ተቀብሮ ነበርና ለእርሱ ፈጽሞ እንደካሰ ለማጠየቅ ፫(3) መዐልት ፫(3) ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ዓለሙን በሞቱ አድኖ ተነሣ። በሰኑይ ዕለት ይሜርየነ ወየሐይወነ ወአመ ሣልስት ዕለት ሥጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ ወአመ ሣልስት ዕለት ንትነሣእ ወንቀውም ምስሌሁ እንዲል ሆሴዕ ፮፣፫።

ተነሥቶም ፵ (40) ቀን መጽሐፈ ኪዳንን ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ለሐዋርያት አስተማረ። እንዲህም ስለሆነ ግን እንደቀድሞው ሰው ሰብስቦ ጉባኤ ሰርቶ ያስተማረ አይደለም ለአንዱም ለሁለቱም ባለሟሎቹ እየተገለጸ ነው እንጂ ማቴ ፳፰: ማር ፲፮፣፳፬: ዮሐ ፳። ዛሬም ምድራዊ ንጉሥ ልሰወር ባለ ጊዜ ሲያሻው ከአዳራሽ ገብቶ ሲያሻው ከእልፍኝ ተከቶ ለአንዱም ለሁለቱም ባለሟሎቹ ሳይገለጥ እንዳይውል ለመላው ግን የተገለጠላቸው **ሦስት** ቀን ነው የትንሣኤ፣ የአግብኦተ ግብር (ዳግም ትንሣኤ) ፣ የጥብርያዶስ (ዓሣ ሲፈልጉ) ወዝንቱ ሣልሱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ያስተርእዮሙ ለአርዲኢሁ ተንሢኦ እምነ ምውታን እንዲል። ዮሐ. ፳፣፲፱። ከዚህ በኋላ ትእዛዙን አዟቸው ተሰፋውን ነግሯቸው ዐረገ ትእዛዙ ሑሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ያለው ነው ማቴ. ፳፰፣፲፱። ተሰፋ ጽንሑ ተስፋሁ ለአብ አንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ያለው ነው ሉቃ ፳፬፣፵፱።

በተነሣ በኃምሳ ቀን ባረገ በአሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት ሰደደላቸው እስከዚያ ወዴት ኑሮ ቢሉ ከአሥረኛው መዓርግ የወጣን እኛ ነበርንና ወደ ጥንት ቦታችን እንደመለሰን ለማጠየቅ።

ቦ ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት አንዱ ነገድ ሥጋዌውን ያላወቁ ነበሩና እነዚያን ሲያስተምር ቆይቶ ምነው ይህማ እንዳይሆን ፈጣሪ ፍጡር ይመስል አንዱን ሥራ ሲሠራ አንዱ ሥራ ይከፈልበታልን ወዲያስ ቢያስተምራቸው ወዲህስ መንፈስ ቅዱስን ቢሰድላቸው ይሆንለት አልነበረምን ቢሉ ነገር ከቀደመው ይገባል።

በ እኔ አሥሩን ቃላት አሥሩን ሕዋሳት ጠብቄ መንፈስ ቅዱስን ሰጠኋችሁ እናንተም አሥሩን ቃላት አሥሩን ሕዋሳት ብትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣችኋል ለማለት።

ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከብልየት ታደሱ በአእምሮ ጎለመሱ ምሥጢር ተረጎሙ ፍሩሃን የነበሩ ጥቡዓን ሆኑ አንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ ፸፪(72) ቋንቋ ይናገሩ ጀመር አንድ ዓመት በጎብረት መዲናይቱ ኢየሩሳሌምን ሲያስተምሩ ኖሩ ወነበሩ ሐዋርያት ዓመተ ፍጽምተ በኢየሩሳሌም እንዲል። ከዚህ በኋላ ሑሩ ወመህሩ ያላቸውን ያውቃሉና ለስብከተ ወንጌል ሲፋጠኑ ይህን ባሕረ ሐሳብ ሳያስተምሩት ቀርተዋል።

በ ድሜጥሮስ እንዲነሣ አውቀው እርሱ ያስተምረዋል ብለው ትተውታል። ከሐዋርያት ቀጥለው የነበሩ ምእመናን ዐቢይ ጾምን በጥር ፲፪ (12) ቀን ጀምረው በየካቲት ፳፩ (21) እየፈጸሙ በዓል ሳይዙ ከጾም ላይ ያርፉ ነበር ሰሙነ ሕማማትንም በመጋቢት ፳፪(22) ጀምረው በ፳፯(27) እየፈጸሙ በ፳፱(29) ትንሣኤን ሰኞም ቢውል ማክሰኞም ቢውል ያከብሩ ነበር ይህም ሥርዓት ሲያያዝ እስከ ዘመነ ድሜጥሮስ ደርሷል። ይህም ድሜጥሮስ ጌታ ባረገ በ፻፹(180) ዘመን በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ሆኖ ተሾመ በተሾመ በ፳፯(27) ዘመን ይህ ባሕረ ሐሳብ ተገለጸለት እርሱም ለ፫ቱ(3) ሊቃነ ጳጳሳት ፭ኛ(4) በኢየሩሳሌም ለነበረው ኤጲስ ቆጶስ ጽፎ ሰደደላቸው እነርሱም ሐዋርያት በዲድስቅልያ ካስተማሩት ጋራ አንድ ቢሆንላቸው ተቀብለው አስተምረውታል።

ሐዋርያት በዲድስቅልያ ምን ብለው አስተምረውታል ቢሉ ወኢይኩን ትንሣኤ ዘእንበለ በዕለተ እሑድ ብለው አስተምረዋል። ሠለስቱ ምዕትም ጉባኤ ሠርተው አስተምረውታል ወአስተላጸቅዋ ለጾመ ፶ ቅድስት ምስለ ሰሙነ ሕማማት ወሠርዑ አበቅቴ ወሐሳበ ውስተ ኵሎን አብያተ ክርስቲያናት እንዲል ቁጥሩም ቢፋለስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ይመስክር ብለዋል ወአዘዙ ከመ ኵሉ ዘስሕተ አበቅቴ ወሐሳበ ይትመራሕ በሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ እንዲል።

ይህን ባሕረ ሐሳብ ሁሉ ሊማረው ይገባል ይልቁንም ካህናት መነኰሳት ሊማሩት ይገባል ባሕረ ሐሳብን የማያውቅ ካህን ውሃ የሌለው ደረቅ ወንዝን ይመስላል ደረቅ ወንዝ ነጋድያን አልፈው ሲሄዱ ጫፉ ረዝሞ ቅጠሉ ለምልሞ ታላቅ ዛፍ ባዩ ጊዜ ውሃ ያለው መስሏቸው ከጥላው ዐርፈን ጥሬ ቆርጥመን ውሃ ጠጥተን እንነሣ ብለው ይሄዳሉ ውሃ ሲያጡበት አዝነው ተሰቅቀው ይመለሳሉ ባሕረ ሐሳብንም የማያውቅ ካህን ምእመናን አምሞ ጠምጥሞ መነሳንሱን ይዞ ሠናፊሉን አንሰርቶ ልብሱን አነጻጽቶ በአዩት ጊዜ የተማረ መስሏቸው አጽዋማትን በዓላትን አውጥቶ ይነግረናል ብለው ሊጠይቁት ይሄዳሉ ፍሬ ነገር ሲያጡበት አዝነው ተሰቅቀው ይመለሳሉ ካህን ወመነኰስ ዘኢተምህረ መጽሐፈ ባሕረ ሐሳብ ይመስል ከመ ፈለግ ዘአልቦ ማይ ውስቴቱ ወከመ ሀገር ዘአልባ ጥቅም እንዲል።

የድሜጥሮስ ታሪክ

የድሜጥሮስንም ነገር ከዚህ ይናገሩታል ትውልዱ ነገዱ ከምእመናነ እስክንድርያ ነው። አርማስቆስ ደማስቆስ የሚባሉ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ ልጆቻቸውም ድሜጥሮስ ልዕልተ ወይን ይባላሉ አርማስቆስ የድሜጥሮስ አባት ነው ደማስቆስ የልዕልተ ወይን አባት ነው አስቀድሞ የልዕልተ ወይን አባት ሞተ ከአጎቷ ቤት ከድሜጥሮስ ጋር አደገች የልዕልተ ወይን አባት ሲሞት ልጇ ልዕልተ ወይንን ከ፲፭(15) ዓመት በታች አታጋቧት ከ፲፭ ዓመት በላይም አታሳልፏት ለአሕዛብ አትስጧት ብሎ ተናዞ ዓረፈ ያን ጊዜ ምእመናን ያነሱበት አሕዛብ የበዙበት ወራት ነበርና ለእርሷ የሚሆን ደግ ሰው አጡ እነርሱም ሕንጻ ሃይማኖት ከሚፈርስ ሕንጻ ሥጋ ይፍረስ ብለው ለአጎቷ ልጅ ለድሜጥሮስ አጭተው አጋቧት ሥርዓተ መርዐዊ ወመርዐት ያድርሱ ብለው ከጫጉላ ቤት አግብተው መጋረጃ ጥለውባቸው ሄዱ እርሷም ወንድሜ እኔን ንቀህ ነው፤ ወይስ ተዘምዶውን አለችው። እርሱም እኔስ አንችንም ተዘምዶውንም ንቄ አይደለም የአባት የእናት ፈቃድ እፈጽማለሁ ብየ ነው እንጂ አሁንም ንጽሕናውን ከወደድሽው አብረን እንኑር የተለያየን እንደሆነ እኔን ለአንዲቱ አንችንም ለአንዱ ያጋቡናል አብረን ብንኖር ግን እግዘአብሔር ልጅ ባይሰጣቸው ነው መክነው ነው ይሉናል እንጂ በዚህ የሚጠረጥረን የለም አላት እሷም ይሁን አለችው።

ከዚህ በኋላ በአንድ አልጋ እየተኙ አንድ ምንጣፍ እያነጠፉ አንድ ልብስ እየለበሱ ፵፰(48) ዘመን በንጽሕና አብረው ኖረዋል ይህም ይታወቅ ዘንድ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ቀኝ ክንፉን ለእርሱ ግራ ክንፉን ለእርሷ አልብሷቸው አድሮ ጧት በአምሳለ ርግብ በመስኮት ወጥቶ ሲሄድ ይታይ ነበር። ድሜጥሮስም ድኮ ታጥቆ ተክል አጽድቆ እርፍ አርቆ የተጣላ አስታርቆ የታመመ ጠይቆ ይኖር ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ወደ ተክል ቦታ ቢገባ ያለጊዜው ያፈራ የስንዴ ዛላ የወይን ዘለላ አገኘ ይህንንስ ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወስጄ በረከት ልቀበልበት ብሎ አሰበ አስቦም አልቀረ ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት እርሷም ይህማ ለአባታችን ለሊቀ ጳጳሱ ነው እንጂ መች ለእኛ ይገባናል ብላ በንጹሕ ሙዳይ አድርጋ እንካ ወስደህ በረከት ተቀበልበት አለችው በፈቃደ እግዘአብሔር የባልና የሚስት ሐሳብ አንድ ሆኗል።

ያንጊዜ ሊቀ ጳጳሱ ዮልዮስ ወይም ዩልያኖስ ይባል ነበር አርጅቶ ነበርና ሕዝቡ ተሰብስበው አባታችን አንተ አረጀህ ወደ ደገኛው ዓለም ልትሄድ ሆነ እኛን የሚጠብቀን ደግ ሰው ተካልን አሉት እርሱም ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመውን እንድናውቀው ቀኖና እንግባ አላቸው። ተያይዘው ቀኖና ገቡ ለእርሱ ዕለቱን ተገለጸለት እነርሱን ሱባዔያቸውን ሲጨርሱ አገኛችሁን አላቸው እኛስ አላገኘንም አሉት እኔ አግኝቼዋለሁ ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው ያለጊዜው ያፈራ የስንዴ ዛላ የወይን ዘለላ ይዞ የሚመጣው ነው አላቸው ወዲያውም ድሜጥሮስ መጥቶ ከበር ቁሞ ንገሩልኝ አለ ግባ በሉት ብሎ አስገብቶ ሕዝቡን አሰባስቦ ያልኳችሁ ሰው ይህ ነው ይቀመጥ በወንበሬ ይናገር በከንፈሬ እሱን ተክቼላችኋለሁ ብሎ በሦስተኛው ቀን ዓረፈ።

ወቀበርዎ በዝማሬ ወበማሕሌት ይላል ገንዘው ቀበሩት እርሱን ቀብረው ሲመለሱ ወንበር ያለ ሹም አያድርምና አባታችን የሰጠን አንተን ነውና ተሾምልን አሉት እርሱም ጳድቁ በተቀመጠበት

ወንበር እኔ ኃጥኡ ድንግሉ በተቀመጠበት ወንበር እኔ ሕጋዊው ምሁሩ በተቀመጠበት ወንበር እኔ ጨዋው መቀመጥ አይገባኝም አይሆንም አላቸው ወአጎዝዎ በኵርሕ ይላል ግድ ብለው ሹመውታል እርሱም ለመንበረ ማርቆስ ፲፪ኛ(12) ተራ ቁጥር ነው በተሾመ ጊዜ የሕዝቡ ኃጢአታቸው ተገልጾ እየታየው አንተ በቅተህል ቁረብ አንተ አልበቃህም አትቁረብ እያለ ይከለክላቸው ጀመር እነርሱም እርሱ በማይገባው ከሚስቱ ጋር ሁኖ እኛን እንዲህ ይለናል እያለ በዚህ ምክንያት ያሙታል ይጠሉታል።

ከዕለታት በአንዱ ቀን የሚሸሩበትን ምክንያት ሲሹ ቀድሞ አባታችን ዮልዮስ አንቀጸ ብፁዐንን አንቀጸ አባግዕን አንብቦ ተርጉሞ ይነግረን ነበር አንተም አባታችን አንቀጸ ብፁዐንን አንቀጸ አባግዕን አንብበህ ተርጉመህ ንገረን አሉት ጨዋ ነው አይሆንለትም በዚህ ምክንያት እንሸረዋለን ሲሉ ነው ለጊዜው ነቢየ እግዘአብሔር ሙሴ በአካለ ነፍስ መጥቶ በእርሱ ተገብቶ አሰምቷቸዋል። ፍጻሜው ግን ብሉይ ከሐዲስ ተገልጦለታል ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ኢትፍቅድ አድጎኖ ርእስከ አላ ክስት ሎሙ ክብረከ ዘሀሎ ማዕከሌከ ወማዕከለ ብእሲትከ ከመ ኢይትጎነሉ ሕዝብ በእንቲአከ ሕዝቡ አንተን እያሙ እንዳይጎዱ ክብርህን ግለጽላቸው አለው።

እርሱም እኔ በማስተዳድረው ሀገረ ስብከት ያላችሁ ምእመናን ሁሉ አንድ አንድ ሸክም እንጨት እየያዛችሁ ተሰብሰቡ ብሎ አዋጅ ነገረ ሕዝቡም አንድ ሸክም እንጨት እየያዙ ተሰበሰቡ ያኑን ደመራ አስደምሮ በእሳት አቃጥሉት ብሎ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ቅዳሴ ገባ ቅዳሴውን ሲጨርስ ልብሰ ተክህኖውን እንደለበሰ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ከእሳቱ ውስጥ እየገባ እየወጣ ያጥን ጀመር።

ቦ ከደመራው ላይ ቁሞ በእሳት አቃጥሉት አላቸው በምን ምክንያት እንሸረዋለን ስንል ከእሳት ገብቶ ሊሞት ነው አሉ ነገር ግን ነበልባሉ በርዶ ፍሕሙ መርቶ ከፍሕሙ ላይ ቁሞ ሲጸልይ አዩት አለሳ አልሞተም አሉ አሁንም አላመኑኝምን ብሎ ሚስቱን ከምቅዋመ አንስት ቁማ ነበረችና አስጠርቶ ንዒ ስፍሒ አጽፈኪ ነይ ኩፋርሽን(ነጠላ) ዘርጊ አላት ነጭ ሐር ልብስ ለብሳ ነበርና ፍሕሙን በእጁ እያፈሰ ከልብሷ ላይ አድርጎ ሂጂ እየዞርሽ ለሕዝቡ ሁሉ አሳዩ አላት እሷም ይኸው ከተጋባን ፵፰(48) ዘመናችን ነው በልማደ ብእሲ ወብእሲት አንተዋወቅም የንጽሕናችንም ምስክር ይህ ነው በከንቱ አትሙን እያለች ለሕዝቡ ሁሉ እየዞረች አሳይታለች ከልብሷም አንድ ዘሀ ስንኳ አልቀነበረም።

ሕዝቡም አ አቡነ ሥረይ ለነ አባታችን በክፉ አምተንህል ይቅር በለን አሉት እርሱም ይፍታሕ ይጎድግ ያንጽሕ ወይቀድስ ወያስተሥሪ ሊቀ ካህናት ሠራዬ ኃጢአት ወደምሳሴ አበሳ ዘወሀቦሙ ሥልጣነ ለአበዊነ ሐዋርያት በዘአእመረ መንፈስ ቅዱስ ይሥረይ ለክሙ ኃጢአተክሙ ዘገበርክሙ እምንዕስክሙ እስከ ይእዜ አበውየ ካህናት ወአኃውየ ዲያቆናት አግብርተ እግዘአብሔር ወአእማተ እግዘአብሔር ኩኑ ፍቱሐነ ወንጹሐነ ይረስየነ ይረስይክሙ ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ብሎ ናዟቸዋል ኑዛዜ ያን ጊዜ ተጀምሯል።

የድሜጥሮስም ጸሎቱ ቀን ቀን ሰባት ሰባት፣ ሌሊት ሌሊት ፳፫ ፳፫ (23 23)ሱባኤ እየሰገደ ይጸልይ ነበር። ስለምን የቀኑ አነሰ የሌሊቱ በዛ ቢሉ ቀን ሲፈርድ ሲተች፣ የተጣላ ሲያስታርቅ፣

የተበደለ ሲያስክስ፣ የተቀማ ሲያስመልስ፣ ድውይ ሲጠይቅ፣ የሞተ ሲቀብር ይውል ነበር በሌሊት ግን ይህ ሁሉ የለበትምና ስለዚህ የቀኑ አነሰ የሌሊቱ በዛ። አጽዋማት በዓላት እንዲህ እንደዛሬው ሁሉ አልተወሰኑም ነበርና ነነዌ ዐቢይ ጾም ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ፣ ደብረ ዘይት ሆሳዕና ትንሣኤ ጰራቅሊጦስ ከእሑድ፣ ስቅለት ከዐርብ፣ ዕርገት ከኃሙስ፣ ርክበ ካህናት ጾመ ድኅነት ከረቡዕ ባይወጡ በወደድኩ ነበር ብሎ ተመኘ።

ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ነገር በተምኔት ይፈጸማልን ሱባዔውን ገድፈህ የተረፈውን ያዝ አለው የቀኑ ሰባት ሱባኤ ቢገጥሙት ፶፱ (48) ይሆናል። ፴(30)ውን ገድፎ ፲፱(19) ይተርፋል። ይህን መጥቅዕ በለው ብሎታል የሌሊቱ ፳፫(23) ሱባኤ ፻፷፩(161) ይሆናል ፻፶ውን(150) በ፭(5) ሠላሳ ገድፎ ፲፩(11) ይተርፋል ይህን አበቅቴ በለው ብሎታል ፲፱ኝና ፲፩ን(19+11) ቢገጥሙት ፴(30) ይሆናል መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቴ ቢያንስ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከ፴(30) አይወጡም ከ፴(30) አይወርደም ሁልጊዜ ፴ ሆነው ይኖራል እንጂ መጥቅዕ ወአበቅቴ እመ ይበዝኑ ኢየዐርጉ እም፴ ወእመ ይውጎዱ ኢይወርዱ እም፴ ወትረ ይከውኑ ፴ እንዲል። እርሱም በእነዚህ እየቀመረ በዓላትን አጽዋማትን አወጣ እንደተመኘ አገኘ።

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ በፀሐይ ፯የሯየ፱ (7519) ዓመት ሆነ በዘመነ ሉቃስ። ለዚህም መስፈሪያ መቁጠሪያ ፯(7) አዕዋዳት ፯(7) መስፈርታት አሉ። ምንና ምን ናቸው ቢሉ ዐውደ ዕለት፣ ዐውደ ወርኅ፣ ዐውደ ዓመት፣ ዐውደ አበቅቴ፣ ዐውደ ፀሐይ፣ ዐውደ ማኅተም፣ ዐውደ ቀመር ናቸው መስፈርታቱም ሳድሲት ኃምሲት ራብዒት ሣልሲት ካልዒት ኬክሮስ ዕለት ናቸው።

ከእነዚህም ሦስቱ በዕለት አራቱ በዓመት ይቆጠራሉ ዐውደ ዕለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት ሰባቱ ዕለታት ናቸው። ዐውደ ወርኅን ለማስገኘት ሁል ጊዜ በሰባት በሰባት ሲመላለሱ ይኖራሉ ዐውደ ወርኅ በጨረቃ አንድ ጊዜ ፳፱(29) አንድ ጊዜ ፴ (30) ነው በፀሐይ ግን ሁል ጊዜ ፴ ሁኖ ይኖራል። ዐውደ ዓመትን ለማስገኘት ሁል ጊዜ በ፴ በ፴(30) ሲመላለስ ይኖራል ዐውደ ዓመት በጨረቃ ፫፻፶፬ (354) ዕለት ነው በፀሐይ ፫፻፷፭(365) ዕለት ነው ፫፻፷፮ (366)ም ይሆናል በዘመነ ዮሐንስ።

ዐውደ አበቅቴ ፲፱(19) ዓመት ነው በዚህ ጊዜ ፀሐይና ጨረቃ ጎዳናቸውን ፈጽመው በተፈጠሩበት ኖኅት ተራክቦ ያደርጉበታል ከዚህም አያይዘው ሊቀ ነቢያት ሙሴ መምህራነ ወንጌል ሐዋርያት ሊቀ ጳጳሳት ድሜጥሮስ ከ፳ ፩ ከ፵ ፪ ከ፷ ፫ ከ፹ ፬ ከ፻ ፭ ከ100 ፮ ከሺው(፼) ፯ እየነሣችሁ ቁጠሩ ማለታቸው ለዚህ ነው። ዐውደ ፀሐይ ፳፰(28) ዓመት ነው በዚህ ጊዜ ዕለት ከወንጌላዊ ይገናኙበታል ዕለቱ ረቡዕ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው ስለምን ዕለቱን ፀሐይ አለው ቢሉ በትእዛዝከ ይቀውም ዕለት እንዲል ስለምን ወንጌላዊውን ፀሐይ አለው ቢሉ አንትሙ ብርሃኑ ለዓለም ካላቸው አንዱ እርሱ ነውና። ዐውደ ማኅተም ፸፮(76) ዓመት ነው በዚህ ጊዜ

አበቅቴ ከወንጌላዊ ይገናኙበታል አበቅቴው ፲፰(18) ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው ዐውደ ቀመር ፭፻፴፪(532) ዓመት ነው በዚህ ጊዜ አበቅቴ ወንጌላዊ ዕለት ይገናኙበታል አበቅቴው አልቦ ወይም (ዜሮ) ወንጌላዊው ማቴዎስ ዕለቱ ሠሉስ ነው።

ዓመተ ወንጌላዊን ለማወቅ መላውን ዓመተ ዓለም ለ፬ቱ ወንጌላውያን ትክክል መድቦ ፩(1) ቢተርፍ ማቴዎስ፣ ፪(2) ቢተርፍ ማርቆስ፣ ፫(3) ቢተርፍ ሉቃስ፣ ትክክል ቢሆን ዮሐንስ ነው።

የዘንድሮን ዓመተ ወንጌላዊ ለማወቅ መላውን ዓመተ ዓለም 7519 / 4 = 1879 ደርሶ 3 ይቀራል ዘመኑ **ዘመነ ሉቃስ** መሆኑ በዚህ ይታወቃል

ጥንተ ቀመርንም ለማወቅ መላው ዓመተ ዓለም ላይ መጠነ ራብዒትን ደምሮ በሰባት መግደፍ ነው 7519 + 1879 = 9397 / 7 = 1342 ደርሶ 4 ይቀራል ጥንተ ቀመር ከማክሰኞ ይጀምራል መስከረም ፩ ዓርብ መዋሉ በዚህ ይታወቃል።

ጥንተ ዮን/ዖን ለማወቅ ከጥንተ ቀመር ላይ ፩ መቀነስ ነው

7519 + 1879 = 9397 / 7 = 1342 ቀሪ 4 - ፩ መስከረም ፩ ዓርብ መዋሉ በዚህ ይታወቃል።

የዘመኑን መደብ ለማውጣት መላውን ዓመተ ዓለም በዐቢይ ቀመር በማዕከላዊ ቀመር በንዑስ ቀመር መቀመር ነው

7519 + 532 = 14 ቀሪ 71 / 19 = 3 ቀሪ 14

7519 + 76 = 98 ቀሪ 71 / 19 = 3 ቀሪ 14

7519 + 19 = 395 ቀሪ 14 በዐቢይም በማዕከላዊም በንዑስም በዚያም በዚህም ቢቀምሩ 14 ይቀራል **14** መደብ ወጣ ይሏል በዘመነ ሉቃስ 2019

የዘመኑን ወንበር ለማግኘት ለመደብ ከወጣልን ላይ አንድ መቀነስ ነው አሐደ አእትት ለዘመን እንዲል ስለምን እንቀንሳለን ቢሎ ስለተጀመረ ተቆጠረ ስላልተፈጸመ ታተተ እንዲል ከ14 ላይ ፩ ስንቀንስ 13 ይቀራል **13** ወንበር ወጣ ይሏል በዘመነ ሉቃስ 2019።

በዘመነ ሉቃስ አበቅቴን ለማግኘት 13 ወንበር አስራ አንድ አስራ አንድ ቢሰጡ 143 ይሆናል።

አበቅቴ

13 * 11 = 143 / 30 = 4 ቀሪ 23 120ውን በአራት ፬ ገድፎ 23 ይተርፋል። **23** አበቅቴ ወጣ ይሏል በዘመነ ሉቃስ 2019

መጥቅዕን ለማግኘት ለ13ቱ ወንበር ፲፱: ፲፱ ቢሰጡ 247 ይሆናል።

መጥቅዕ

13 * 19 = 247 / 30 = 8 ቀሪ 7 240ን በሰባት ፴ ገድፎ 7 ይተርፋል። **7** መጥቅዕ ወጣ ይሏል በዘመነ ሉቃስ 2019

7 መጥቅዕንና 23 አበቅቴን ቢገጥሙት ፴ ይሆናል። መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቴ ቢያንስ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከሠላሳ አይወጡም ከሠላሳ አይወርደም። ሁልጊዜ ፴ ሆነው ይኖራሉ እንጂ። መጥቅዕ ወአበቅቴ እመ ይበዝኑ ኢየዐርጉ እም ሠላሳ ወእመ ይውጎዱ ኢይወርዱ እምሠላሳ ወትረ ይከውኑ ሠላሳ እንዲል። የሚነሣው ዕለት የሚነሣለት ዓመት ነው አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው ቢሉ ጐልቆ ተረፈ ዘመን ማለት ነው አበቅቴ ብሂል ዘበትርጓሜሁ ጐልቆ ተረፈ ዘመን እንዲል። ጨረቃ ከፀሐይ ፲፭ ታጎድላለችና።

መጥቅዕ ማለትሳ ምን ማለት ነው ቢሉ በቁሙ መጥቅዕ ደወል ነጋሪት ማለት ነው መጥቅዕ ነጋሪት ሲመታ ብዙ ሰው እንዲሰበሰብ እርሱም አጽዋማትንና በዓላትን ሰብስቦ የሚያውል ስለሆነ መጥቅዕ ብሂል አስተጋባኢ ብሂል እንዲል። እንዲህ ከሆነ ስለምን ዕለቱን መጥቅዕ አለው ቢሉ እስራኤል ፮ ዓመት ምድራቸውን አርሰው በ፯ኛው ዓመት በመጀመሪያው ወርኅ በ፲፱ኛው ቀን መጥቅዕ (ነጋሪት) መትተው ሕዝቡን ሰብስበው ጉባኤ ሠርተው በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማት በዓላትን አውጥተው ይለያዩ ነበር መምህራነ ቤተክርስቲያንም የቅዱስ ዮሐንስ ዕለት መጥቅዕ (ነጋሪት) መትተው ሕዝቡን ሰብስበው ጉባኤ ሠርተው በዘመነ ሐዲስ የተሠሩ አጽዋማት በዓላትን አውጥተው የሚለያዩ ስለሆነ እንዲህ አለ። እስመ ከመ መጥቅዕ ዘብርት ወዘጎሚን ዘዕፅ ወዘዕብን ያስተጋብእ ዝርዋነ(ሰብአ) ከማሁ ውእቱኒ ያስተጋብእ አጽዋማተ ወበዓላተ ዘኵሎን ዓመታት(ለለኩሉ ዓመት) እንዲል።

መጥቅዕ ፲፬ትን አይነካም። ከ፲፬ በላይ ከሆነ መጥቅዕ በመስከረም ይውላል። ነነዌ በጥር ትውላለች። እንዲህ ስለሆነ ግን መባጃ ሐመር ፴ መልቶ ቢተርፍ ፴ውን ገድፎ በተረፈው ቆጥሮ ነነዌ በየካቲት ትውላለች። አልቦ አበቅቴ በሆነ በ፲፭ኛው ዓመት ይገኛል። ከ፲፬ በታች ከሆነ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል ነነዌ በየካቲት ትውላለች። በ፭ እና በ፲፬ መጥቅዕ አይውልም ዘይገብር አሐደ መጥቅዐ ንፉቅ ወስሑት ውእቱ እንዲል ዮሐንስ አቡሻህር። የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ይጀምራል። የቅዳሜ ተውሳክ ፫ ነው። የእሑድ ተውሳክ ፪ ነው። የሰኞ ተውሳክ ፮ ነው። የማክሰኞ ተውሳክ ፩ ነው። የረቡዕ ተውሳክ ፬ ነው። የኃሙስ ተውሳክ ፫ ነው። የዐርብ ተውሳክ ፮ ነው።

መባጃ ሐመር

መጥቅዕ ከ14 በላይ ቢሆን በጥቅምት ይውላል ከ14 በታች ቢሆን በመስከረም ይውላል 14 አይነካም “መጥቅዕ ቢበዛ በመስከረም ንዛ መጥቅዕ ቢያንስ በጥቅምት ዳስስ” እንዲሉ መምህራን

7 + 8 = 15

ሰኞ የካቲት 15 **ጾመ ነነዌ**

14 + 15 = የካቲት 29 **ዐቢይ ጾም**

11 + 15 = መጋቢት 26 **ደብረ ዘይት**

2 + 15 = ሚያዝያ 17 **ሆሳዕና**

የፍስሕን ነገር ከዚህ ይናገሩታል ለፍስሕ የዕለት ተውሳክ አትሻም በደረቅ መጥቅዕ ትወጣለች መጥቅዕ 7 የፍስሕ ተውሳክ 10 አንድ ላይ ቢገጥሙት 17 ይሆናል እሑድ ሚያዝያ 17 የአይሁድ ፋሲካ ይውላል በዓሉን አናከብረውም ስለምን እናወጣዋለን ቢሉ ሐዋርያት ፍስሕን ከትንሣኤ ጋራ አንድ አድርጎ ያዋለ ካህን ከክህነቱ ይሻር ምእመን ቢሆን ከምእመናን ይለይ ብለው አውግዘዋልና ለይተን እናወጣዋለን ይህ አምሳል መርገፍ ሆኖ ቀርቷልና።

7 + 15 = ሚያዚያ 22 **ስቅለት**

9 + 15 = ሚያዚያ 24 **ትንሣኤ**

3 + 15 = ግንቦት 18 **ርክበ ካህናት**

18 + 15 = ሠኔ 3 **ዕርገት**

28 + 15 = ሠኔ 13 **ጰራቅሊጦስ**

29 + 15 = ሠኔ 14 **ጾመ ሐዋርያት**

1 + 15 = ሠኔ 16 **ጾመ ድኅነት**

እስከዛሬ ድረስ ቅዱስ ማርቆስ ምግብናውን ሲያደርግ ነበር ከእንግዲህ ቅዱስ **ሉቃስ** ምግብናውን ይጀምራል።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ሃሌ ሉያ በዘንዜከር ሐሳባተ ሕጉ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ሉቃስ ወንጌላዊ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ዮሐንስ ዜናዊ ምነው ሉቃስን ወንጌላዊ አለው ቢሉ ባለዘመን ነውና ምነው ዮሐንስን ዜናዊ አለው ቢሉ የሚያመጣ ነውና። በ፸፻ ወበ፷፻፲፱ ኮነ ዓመተ ዓለም። በ፶፻፷፻ ኮነ ዓመተ ፍዳ ወዓመተ ኵነኔ። በ፳፻፲፱ ኮነ ዓመተ ምሕረት ዮም ሠረቀ ለነ ወርኅ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት በሰላመ እግዘአብሔር አብ አሜን።

ሕጸጽ ፩ አበቅቴ ፳፫ ሠርቀ መዐልት ፩ ፡- ፳፭ ሠርቀ ሌሊት፣ ፩ ሠርቀ መዐልት፣ ፳፱ ሠርቀ ወርኅ፣ ፮ ጥንተ ዕለት፣ ፬ ጥንተ ቀመር፣ ፫ ጥንተ ዮን።

ዮም በዛቲ ዕለት ዘአቅረብነ ለከ አምኃ ስብሐት ያዕርጉ ለነ መላእክት ተወከፍ ለነ

እግዚአ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን አነሣስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን አሜን።